# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

በዚህ ዕለት ብርሃን እውራን ተስፋ ቅቡጻን መዋኤ ጋኔን አምላክ ብርሃን ስለመሆኑ ዕውራንን በሽተኞችን ስለማዳኑ ይዘመራል።

## የዕለቱ ምስባክ

ደቂቀ እጓለእመሕያው እስከ ማዕዜኑ ታከብዱ ልበክሙ
ለምንት ታፈቅሩ ከንቶ ወተሐሡ ሐሰተ
አእምሩ ከመ ተሰብሐ እግዚአብሔር በጻድቁ

እናንተ የሰው ልጆች እስከ መቼ ድረስ ልባችሁን ታከብዳላችሁ
ከንቱ ነገርንስ ለምን ትወዳላችሁ ሐሰትንስ ለምን ትሻላችሁ
እግዚአብሔር በጻድቅ እንደተገለጠ (ተመሰገነ) እወቁ።

መዝ 4፤2-3

ወንጌል፥ ዮሐ ፱፤፩ እስከ ፍጻሜው
ቅዳሴ፥ የጌታችን ቅዳሴ (ነአኵተከ)

ዘመነ አስተርእዮ የሚባለው ከጥር ፲፩ እስከ ጥር ፴ ቀን ድረስ ያሉት ዕለታትና ሳምንታት ናቸው። ... በእነዚህ ዕለታትና ሳምንታት የሚዘመረው መዝሙር አንሰሰወ አስተርአየ ተወለደ ተጠመቀ ከበካብ ማይ መርዓዊ የሚሉ ይሆናሉ። ዘመነ አስተርእዮ የተባለበትም ምክንያት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ በእስራኤል አውራጃ እየዞረ በመምህርነት ስለተገለፀ አስተርእዮ ወይም በዓለ ኤጲፋንያ ተባለ። ይኸውም አስተርአየ (ተገለጠ) አስተርእዮ (መገለጥ) ማለት ሲሆን ኤጲፋንያ የሚለው ቃል ደግሞ ምስጢሩ ያው ሆኖ ቃሉ ግሪክኛ ነው።

## የዕለቱ የቅዳሴ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ያቤሉ እስራኤል ኢርኢነ ወኢሰማዕነ ዘእውሩ ተወልደ (እስራኤል ዕውር ሆኖ የተወለደ ሰው አሁን ቀደም አላየንም አልሰማንም አሉ።)

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ፩ኛ ቆሮ ፪፤፩ እስከ ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ዮሐ ፩፤፩-፮ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፩፤፴፬ እስከ ፍጻሜ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

### ጌታ ሆይ አምናለሁ።
(ዮሐ ፱፤፴፰)

የዕለቱ ወንጌል ቀልጭ ያለ ማብራሪያ የማያስፈልገው በመሆኑ ወይንም ከሚሰጠው ማብራሪያም በበለጠ የወንጌል ቃሉ (ዘሩ) ስለሚጠቅም አንባቢ ምዕራፉን በሙሉ በማስተዋል ቢመለከተው የበለጠ ይጠቅማል። ይህን ቃል የተናገረው ሰው አስቀድሞ የእግዚአብሔር ክብር ይገለጥበት ዘንድ ዕውር ሆኖ የተወለደ ከጊዜ በኋላ የታወረ ሳይሆን ዕውር ሆኖ የተፈጠረ ሰው ነው (ቁጥር ፩-፱)። መድኃኒታችን ይህንን ሰው ሲያይ በዓይን የሚታይ በሥጋ ላይ የሚፈጸም የተአምራት ሥራውን የማይሠራበት ዕለተ ሞቱን እያስታወሰ «በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ» ብሎ በምራቁ ያራሰውን ጭቃ ቀብቶ እንዲታጠብ አዝዞ ዓይኑን አበራለት (ቁጥር ፮-፲፪)። ያም ቀን ሰንበት ነበርና ለማይረባ አእምሮ የተሰጡ የአይሁድ መምህራን «ይህ ሰው ሰንበትን አያከብርምና ከእግዚአብሔር አይደለም» አሉ። ይሁን እንጂ ኃጢአተኛ ሰው እንደነዚህ ያሉ ተአምራቶችን (ምልክቶችን) ሊያደርግ እንዴት ይችላል የሚሉ ባለአእምሮ ሰዎችም አልታጡም (ቁጥር ፲፫-፲፯)። መለያየት ሆነ። እውሩም ሲጠየቅ «ነቢይ ነው» ብሎ ተናገረ።

አይሁድም የእግዚአብሔርን ማዳን ለመጠራጠር የሚያስችል ነገር ቢያጡ የዕውሩን ሰው ዕውር ሆኖ መወለድ ተጠራጠሩና የዕውሩን ወላጆች ፈልገው «ዕውር ሆኖ ተወለደ የምትሉት ልጃችሁ ይህ ነውን? ታዲያ እንዴት ያያል?» ብለው ጠየቋቸው። ኢየሱስን ክርስቶስ ብሎ የሚያምን ከምኩራባችን ይሰደድ ብለው አይሁድ የወሰኑት ከንቱ ውሳኔ ያሰጋቸው ወላጆችም «ይህ ልጃችን እንደሆነ እውርም ሆኖ እንደተወለደ እናውቃለን። ዳሩ ግን አሁን እንዴት እንዳየ አናውቅም። ወይንም ዓይኖቹን ማን እንደከፈተ እኛ አናውቅም። ጠይቁት እርሱ ሙሉ ሰው ነው ስለ ራሱ ይናገራል።» ብለው የእግዚአብሔርን ተአምር ከመመስከር ዝም አሉ። ስለ ኢየሱስ ባለመናገር የሙኩራብ ኑሯቸውን አራዘሙ፤ ከፈሪሳውያን ግልምጫም ተረፉ። ሃይማኖት እምቢ ያላቸው ፈሪሳውያንም ደግመው ጠርተው «እኛ ይህ ሰው ኃጢአተኛ እንደሆነ እናውቃለን» አሉት። ለእግዚአብሔር ክብር መገለጫ ሆኖ የተፈጠረው ሰው ግን «ኃጢአተኛ መሆኑን አላውቅም» አላቸው። እየደጋገሙ «እንዴት?» « በምን ዓይኖችህን ከፈተልህ» እያሉ ቢዘበዝቡት «ደቀ መዛሙርቱ ለመሆን ትወዳላችሁን?»ብሎ ስላናደዳቸው «እኛስ የሙሴ ደቀ መዛሙርት ነን» ብለው ራሳቸውን ሲያከብሩ እርሱን ግን «አንተ የእርሱ ደቀ መዝሙር ሁን» ብለው ሰደቡት፤ አይገርምም? ወይ አለማወቅ።

ፈሪሳውያን በትንቢቱ ተጠቃሚዎች አይሆኑም እንጂ ትንቢት መናገር ይሳካላቸዋል። እንደ ሊቀ ካህናቱ ቀያፋ ጥሩ ትንቢት ተናግረዋል። የእነርሱንም ታላቅነት ከሙሴ አንጻር ሲገልጡ ሙሴን እግዚአብሔር ተናገረው። ይህን ሰው ግን ከወዴት እንደመጣ አናውቅም አሉት። ለእግዚአብሔር ክብር የተፈጠረው ሰውም «ከወዴት እንደሆነ አለማወቃችሁ ድንቅ ነገር ነው። ዳሩ ግን ዓይኖቼን ከፈተ፤ ከእግዚአብሔር ባይሆን ምንም ሊያደርግ ባልቻለም ነበር ብሎ ክብሩን መሰከረ። እነርሱ ግን «አንተ ሁለንተናህ በኃጢአት ተወልደህ አንተም እኛን ታስተምረናለህን?» ብለው ተናደው ከምኩራብ ውጭ በማይሠራው ስልጣናቸው ከምኩራብ አስወጡት። የእግዚአብሔርን ክብር የሚመሰክረው ከምኩራብና ከቤተ መቅደስ ተባረረ። ለራሳቸው ክብር የቆሙት ከምኩራብ ውስጥ ቀሩ። የዚህን ምኩራብ ፍጻሜ ያየ ሰው! የምድራውያን መቅደስ በር ለተዘጋበት የሰማያዊው መቅደስ በር ተከፈተለት (ዮሐ ፱፤፲፱-፴፱)። እውነትና መንገድ የሆነ ጌታ ወደ ውጭ እንዳወጡት አውቆ ተቀበለው። መድኃኒታችንም «አንተ ሰው በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን?» አለው። እርሱም «... ጌታ ሆይ አምናለሁ።» አለ። የክብር ጌታም «የማያዩ እንዲያዩ የሚያዩትም እንዲታወሩ እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጥቻለሁ።» አለ... ክብር ለእርሱ ይሁን።

ተመልካች ፈሪሳውያንም «እኛ እውሮች ነንን?» አሉት። ኢየሱስም «እውሮችስ ብትሆኑ ኃጢአት ባልሆነባችሁም ነበር (የሥጋ እውርነት ከመንግሥተ ሰማይ አይወጣምና) አሁን ግን እናያለን ትላላችሁ ኃጢአታችሁ ይኖራል» አላቸው።

ለብርሃነ እውራን ተስፋ ቅቡጻን፣ ኃይለ ድኩማን ጌታ ክብር ይግባው። አሜን።